# መንታ መንገድ

ከጌትነት

ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል
ከባህር ከሠይጣን የትኛው ይሻላል

መንታ መንገድ ቆመ ወገኔን ቸገረው
ከአረመኔ አምልጦ አረመኔ በላው

በኛው በአገራችን ሲሸቅል የኖረ
ቸርቻሪ ነጋዴ አረብ ቤት ነበረ
ዛሬ ቂም ሊወጣ ተነሳ በአገር
አረብ ይውጣ ብለን አባረነው ነበር

ጀግና ሕዝብ ሲደፈር እንዴት አይቆጣ?!
የውስጡ ሳያንሰው በውጭም ባላንጣ
የእሱነቱ ትርጉም፣ የዜግነት ክብሩ፣
የደምም ሥጋ ውህደት የነፍስያ ክሩ
እንዳሸበረቀው በሶስት ቀለማቱ፣
ተቀጥቅጦ ሲሆን ባዕድ ምድር ሞቱ፣
ለምን አይፈነዳም፣ ሆኖ ገሞራ እሳት፣ የውስጥ ስሜቱ?!
ለምን አይፈነዳም ጠራርጎ ሲጥለው በሃያል እሳቱ፣
ከውስጥም ከውጭም አላስኖረው ካለ ያን ያህል ጠላቱ?!

መሃል ላይ በመቆም ዜጋችን ተጨንቋል፣
ከአንዱ አምልጦ ባንዱ አበሳውን ያያል!
ጀሮ ዳባ ልበስ ማለቱ ይበቃል
የግፍ የጣር በትር ሞልቶ ተርፎ ፈሷል

13, ኖቬምበር 2013